ዜና
# አመዝኤ



# አዲሱ ሚሌኒየም የኢትዮጵያ ሕዳሴ ይሆናል!!

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ ቅፅ 13 ቁጥር 9 ነሐሴ 1999

## በዚህ ዕትም ውስጥ

በሐምሌና ነሐሴ ወራት ከ154 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሰራጭቷል::
ገጽ 2

በ1999 በጀት ዓመት ከ1.3 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሰራጭቷል::
ገጽ 4

የኤጀንሲው ሠራተኞች የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አካሔዱ::
ገጽ 5

## የአሜሪካን መንግሥት በጎርፍ አደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ ጀልባዎችና ሌሎች ቁሳቁሶችን ለገሠ

የአሜሪካን መንግሥት ድንገተኛ ደራሽ ጎርፍ እና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋዎች በሚከሰቱበት ጊዜ ለሕይወት ማዳን ሥራ የሚያገለግሉ ጀልባዎችና ሌሎች በጎርፍ አደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በአሜሪካን ዓለም አቀፍ የልማትና ተራድዖ ድርጅት /ዩ.ኤስ.ኤ.አይዲ/ በኩል ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ለግሷል::

ይኸንኑ ዕርዳታ የአሜሪካን ዓለም አቀፍ የልማትና ተራድዖ ድርጅት ሚሽን ዳይሬክተር ሚ/ር ግለን አንደርስ ነሐሴ 24 ቀን 1999 ዓ.ም ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ አስረክበዋል::



በአሜሪካን መንግሥት የተለገሠው ይኸው ዕርዳታ 16 በአየር የሚሞሉ ባለሞተር ጀልባዎች ፣ 160 በውኃ ላይ መንሳፈፊያ የነፍስ አድን ጃኬቶች ፣ መጠናቸው 4 ሜትር በ 5 የሆነ 1,100 ጥቅል ኘላስቲክ ሺቶች እና 2,500 ብርድ ልብስ ሲሆን፣ የነዚህ ቁሳቁሶች ጠቅላላ ዋጋ 825 ሺህ 354 የአሜሪካን ዶላር እንደሚሆን በርክክቡ ወቅት ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል::

የአመዝኤ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ዕርዳታውን በተረከቡበት ወቅት ባደረጉት ንግግር የአሜሪካን መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በሚከሰቱ አደጋዎች ሳቢያ ተጎጂ ለሚሆኑ ወገኖች መርጃ ለሚቀርቡ ዓለም አቀፍ የዕርዳታ ጥሪዎች ፈጣንና ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት በግንባር ቀደምትነትና በአርአያነት ከሚጠቀሱት መንግሥታት አንዱ መሆኑን አስታውሰዋል:: አያይዘውም የጎርፍ አደጋ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ ስጋት እየሆነ በመጣበት በአሁኑ ወቅት የተለገሡት እነዚህ ቁሳቁሶች ደግሞ በጎርፍ አደጋ ወቅት የተጠቂ ወገኖችን ሕይወት ለማዳን በሚደረገው ጥረት የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ከፍተኛ

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት
ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት
የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣www.dppc.gov.et

ዜና አመዝኤ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው

"የለማችና የበለፀገች አገር በመገንባት የኢትዮጵያን ገጽ ለመቀየር ቆርጠን ተነስተናል"
ብሩህ ተስፋ መቻቻል ለዴሞክራሲያዊ በህልና አስተሳሰብ

እንደሆነ የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ ይኸን መሰሉ የአሜሪካን መንግሥትና የልማት ኤጀንሲው አጋርነት ወደፊትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያላቸውን እምነት ገልፀው ለተለገሠው ዕርዳታ በኢትዮጵያ መንግሥት፣ በተረጂ ወገኖችና በራሳቸው ስም ምስጋና አቅርበዋል።

የዩኤስ.ኤ.አይዲ ሚሽን ዳይሬክተር ሚ/ር ግለን አንደርስ በበኩላቸው መንግሥታቸውና የኢትዮጵያ መንግሥት በሰብዓዊ ዕርዳታና በኢትዮጵያ ውስጥ ድህነትን ለመቀነስ በሚደረጉ ጥረቶች በሚያደርጓቸው የትብብር ጥረቶች ጉልህና ተስፋ የሚጣልባቸው ለውጦች እየታዩ መሆኑን አመልክተው የአቅም ግንባታ ዕርዳታውና የልማት ትብብሩ ከዚህ በላቀ ደረጃ እንደሚቀጥል እምነቴ ነው ብለዋል።

## በሐምሌና ነሐሴ ወራት ከ155 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሰራጭቷል።

◆ **ለጎርፍ አደጋ ተፈናቃዮች ከ65 ሺህ በላይ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ተከፋፍለዋል።**

በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ከድርቅ ጋር በተያያዘ በምግብ እጥረት፣ በጎርፍ እና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋ እና ሌሎች አደጋዎች ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ባለፉት ሐምሌና ነሐሴ ወራት 1999 ዓ.ም በጠቅላላው 155 ሺህ 967 ኩንታል የምግብ የተሠራጩ መሆኑን ከተገኘው መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል።

በየክልሉ የሚሠራጨው የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ በጥናት ላይ ተመስርቶ በየአካባቢው እንደደረሰው አደጋ ስፋት እና የጉዳት መጠን እንዲሁም የአስቸኳይ ጊዜ



ዕርዳታ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት መሠራጨቱን ከኤጀንሲው የዕርዳታ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በሁለቱ ወራት ከተሠራጨው ጠቅላላ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ውስጥ 107 ሺህ 953 ኩንታል በሐምሌ ወር ቀሪው 48 ሺህ 014 ኩንታል ደግሞ በነሐሴ ወር ዕርዳታ ማግኘት እንደሚገባው ህዝብ ብዛት የሚለያይ ነው። በዚሁ መሠረት በሐምሌ ወር ለድርቅ ተጎጂዎችና ለጎርፍ አደጋ ተፈናቃዮች ከተሠራጨው ጠቅላላ 107 ሺህ 953 ኩንታል ውስጥ ለሱማሌ 78 ሺህ 798.5 ኩንታል ፣ ለኦሮሚያ 9 ሺህ 85 ኩንታል፣ ለአማራ 5 ሺህ 777.5 ኩንታል ፣ ለጋምቤላ 5 ሺህ 714 ኩንታል፣ ለአፋር 3ሺህ 594 ኩንታል ፣ ለደቡብ 1 ሺህ 737 ኩንታል ፣ ለድሬዳዋ 1ሺህ 687 ኩንታል፣ ለትግራይ 1ሺህ 337 ኩንታል እና ለቤንሻንጉል ጉሙዝ

" የልማት ፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባ ፣ የመልካም አስተዳደር ስኬቶቻችን እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ፣ ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶቻችንን በማስተዋወቅ ገጽታችንን እንገንባ " አፍሪካወያን ለአህጉራችን ትንሳኤ እንረባረብ!!

223 ኩንታል ተሠራጭቷል::

በተመሳሳይም በነሐሴ ወር ከተሠራጨው ጠቅላላ 48 ሺህ 14 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለኦሮሚያ 9 ሺህ 994 ኩንታል ፣ ለትግራይ 9 ሺህ 331 ኩንታል ፣ ለአማራ 10 ሺህ 106.5 ኩንታል ፣ ለደቡብ 8 ሺህ 66.6 ኩንታል ፣ ለአፋር 6ሺህ 620 ኩንታል እና ለጋምቤላ 3 ሺህ 897 ኩንታል የተሠራጨ መሆኑ ታውቋል::

በሁሉም ክልሎች ለሚገኙ የአደጋ ተጎጂዎች የተላከው የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ የምግብ እህል ፣ የምግብ ዘይት ፣ ጥራጥሬ እና አልሚ ምግብን ያካተተ መሆኑንም ከተገኘው መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል::

ይኸ በዚህ እንዳለም የክረምቱ ዝናብ ከብዶ በጣለባቸው አንዳንድ የአማራ ፣ ደቡብ ፣ ትግራይ ፣ አፋር ፣ ጋምቤላ እና ኦሮሚያ ክልሎች ወረዳዎች በድንገተኛ ደራሽ ጎርፍ እና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ከምግብ ዕርዳታው በተጨማሪ የተለያዩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ተልከዋል::

በዚሁ መሠረት ከሐምሌ አጋማሽ እስከ ነሐሴ ወር መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ለጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች በጠቅላላው በቁጥር 65 ሺህ 208 የመጠለያ እና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች በስድስቱ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ 17 ወረዳዎች ውስጥ በደረሱ የጎርፍ አደጋዎች ተጎጂ ወገኖች ተሠራጭተዋል::

ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ዕርዳታ መጠንም በየክልሉና በየወረዳዎች እንደደረሰው የጎርፍ አደጋ ስፋትና የተጎጂ ሕዝብ ብዛት ተመድበው ከተሠራጩት ጠቅላላ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ሀሮ ሊሙ ወረዳ ለሚገኙ የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች መጠናቸው 4×5 የሆነ 2000 ፕላስቲክ ሽቶች ፣ በቁጥር 4000 ፕላስቲክ ኩባያ ፣ 4000 ፕላስቲክ ሳህን፣ 4330 ብርድ ልብስ ፣ 2360 ጀሪካን ፣ 2360 ጆግ እና 2360 ብረት ድስት ፣ በጋምቤላ ክልል ኢታንግ ፣ ላሬ እና ጋምቤላ ወረዳዎች በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ መጠናቸው 4×5 የሆነ 3351 ፕላስቲክ ሺት ፣ በቁጥር 1755 ፕላስቲክ ሳህን ፣ 1755 ፕላስቲክ ኩባያ ፣ 1500 ብርድልብስ እና 3351 ጀሪካን ተንገዞ ለተጎጂዎች ተከፋፍሏል፣ በአማራ ክልል በቋራ ፣ ሊቦ ከምከም ፣ ቆቦ ፣ ደራ እና አንጸኪያገምዛ ወረዳዎች መጠናቸው 4×5 የሆነ 1361 ፕላስቲክ ሺት በቁጥር 6087 ፕላስቲክ ሳህን ፣ 6087 ፕላስቲክ ኩባያ ፣ 2518 ጀሪካን ፣ 200 ድንኳን እና 2243 ብረት ድስት እና 2332 በርድ ልብስ በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ተሠራጭቷል በደቡብ ብ.ብ ህዝቦች ክልል በሁምቦ ፣ ምዕራብ አባያ ፣ ቦንኬ እና ሉካ አባያ ወረዳዎች ለሚገኙ የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች መጠናቸው 4×5 የሆነ 444 ፕላስቲክ ሺት ፣ 3620 ፕላስቲክ ሣህን ፣ 3620 ፕላስቲክ ኩባያ ፣ 1026 ብርድ ልብስ ፣ 513 ጀሪካን ፣ 689 ጆግ እና 94 ብረት ድስት ተደልድሎ ተሰጥቷል፣ በትግራይ ክልል ለክልዕተ አውላሎ ወረዳ የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች መጠናቸው 4×5 የሆነ 55 ፕላስቲክ ሺት 237 ፕላስቲክ ኩባያ ፣ 110 ብርድ ልብስ ፣ 55 ጭልፋ ፣ 55 ጀሪካን ፣ 55 ጆግ እና 55 ብረት ድስት ፣ በአፋር ክልል በአባላ ፣ ኤሌዳር እና አዋሽ ፈንታሌ ወረዳዎች በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ መጠናቸው 4×5 የሆነ 660 ፕላስቲክ ሺቶች እና 25 ድንኳኖች መላካቸውን ከዕርዳታ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ክትትል መመሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

አመዝኤ

" የልማት ፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባ ፤ የመልካም አስተዳደር ስኬቶቻችን እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ፤ ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶቻችንን በማስተዋወቅ ገጽታችንን እንገነባ "

# በ1999 በጀት ዓመት ከ1.3 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተሰራጭቷል፡፡

በ1999 በጀት ዓመት በተለያዩ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሳቢያ ጉዳት ደርሶባቸው የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና መንግሥታዊ ባልሆኑ የረድዔት ድርጅቶች አማካይነት በጠቅላላው 1 ሚሊዮን 374



ሺህ 960 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተሠራጭቷል፡፡

ከተጠቀሰው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 1 ሚሊዮን 276 ሺህ 960 ኩንታል መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ለድርቅ አደጋ ተጎጂዎች የተሠራጨ ሲሆን ቀሪው 98 ሺህ ኩንታል ደግሞ በኤጀንሲው አማካይነት በ1998 ዓ.ም መጨረሻ እና በ1999 ዓ.ም ጥቅምት ወር በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በደረሱ የጎርፍ አደጋዎች ተጎጂ ለሆኑ ወገኖች የተሰራጨ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በምግብ ዋስትና ቢሮ በኩል በ6 ክልሎች ለሚካሔደው የሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚሆን 2 ሚሊዮን 187 ሺህ 140 ኩንታል የምግብ እህል በኤጀንሲው በኩል ተጓጉዞ ወደየማሰራጫ ጣቢያዎች እንዲደርስ መደረጉን የኤጀንሲው የበጀት ዓመት የሥራ ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት ሰነድ አመልክቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ በድርቅ ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች ለመርዳት ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በቀረበው የዕርዳታ ጥያቄ መሠረት 803 ሺህ 160 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ እና እንዲሁም ምግብ ነክ ላልሆኑ ፍላጎቶች 38 ሚሊዮን 373 ሺህ 807 የአሜሪካን ዶላር ከለጋሾች ተገኝቷል፡፡

በጎርፍ አደጋዎች ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቃይ የሆኑ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም ከሀገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በዕርዳታ ለማሰባሰብ ተከታታይ ጥሪቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም መሠረት በሀገር ውስጥ ከተደረጉ የተለያዩ የዕርዳታ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ከነሐሴ ወር 1998 አስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከሀገር ውስጥ ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎችና መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ፤ እንዲሁም በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከብር 56 ሚሊዮን በላይ በጥሬ ገንዘብ እና ከብር 15 ሚሊዮን በላይ የሚገመቱ የዓይነት ዕርዳታ ለማሰባሰብ የተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

በተመሳሳይም በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ለዕለት ዕርዳታና መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ

በአዲሱ ሚሌኒየም የሴቶችን እኩል ተሳፊነትና ተጠቃሚነት በተግባር እናረጋግጥ !

በአዲሱ ሚሌኒየም ኢትዮጵያእንን ከሁሉም በሁሉም ተመራጭ ሀገር እናድርጋት



ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በቀረበው የዕርዳታ ጥሪ መሠረት 22 ሚሊዮን 324 ሺህ 283 የአሜሪካን ዶላር ተገኝቶ ለተፈለገው ዓላማ እየዋለ መሆኑን ሪፖርቱ አብራርቷል ፡፡

በ1994/95 ዓ.ም በሀገራችን ተከስቶ የነበረውን አስከፊ የድርቅ አደጋ ለመከላከል የተደረገውን ጥረት ለማገዝ በበጎ ፍቃደኛ ወገኖች ተቋቋሞ የነበረው «አንድ ብር ላንድ ወገን» አሰባስቦት በባንክ ገቢ የተደረው 8.26 ሚሊዮን ብር ለጎርፍ ተጎጂዎች እንዲውል ከአመዝኤ ጋር በጋራ በወሰኑት መሠረት የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም ከሀገር ውስጥና ከውጭ ከተገኘው የገንዘብ ዕርዳታ ጋር ተዳምሮ በሦስት ዙሮች በአጠቃላይ ብር 61 ሚሊዮን 265 ሺህ 391 ከ56 ሳንቲም ለተለያዩ የጎርፍ አደጋ ተጎጂ አካባቢዎች ተደልድሏል፡፡ በዚህም መሠረት ለድሬዳዋ ብር 29 ሚሊዮን 220 ሺህ 797 ከ97 ፣ ለደቡብ ኦሞ ዞን ብር 15 ሚሊዮን 356 ሺህ፣ ለአማራ ክልል ብር 6 ሚሊዮን 582 ሺህ 493 ከ51 ፣ ለሶማሌ ብር 5 ሚሊዮን 851 ሺህ 904 ከ36 ተደልድሎ በዘርፉ በተደረጉ ጥናቶች መሠረት ቅድሚያ ለተሠጣቸው የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እየዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

## የኤጀንሲው ሠራተኞች የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አካሔዱ፡፡

የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ሠራተኞች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥር የሚገኙት የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር እና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር ሠራተኞች የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር አካል በሆነው የሁለት ዛፍ ለሁለት ሺህ ፕሮጀክት ላይ ተሳታፊ ለመሆን ሐምሌ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በየካ ክፍለ ከተማ አንቆርጫ ጠርክ ላይ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አካሂደዋል፡፡

በችግኝ ተከላ ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ባስተላለፉት መልዕክት የበረሀማነት ችግር የመላው ዓለም ሀገሮች በተለይም ጓላቀር የሆኑ የአፍሪካ ሀገሮች ሥጋት በሆነበት በአሁኑ ወቅት የችግኝ ተከላ ፕሮግራሙ ለኛም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ የልማትና የእድገት ብቻ ሳይሆን የህልውናም መሠረት በመሆኑ ሁላችንም እንደግል ጉዳያችን ልንመለከተው ይገባል ብለዋል፡፡ በማያያዝም ዋና ዳይሬክተሩ የሚተከሉት የዛፍ ችግኞች አድገው ለትውልድ ቅርስነት መተላለፍ ያለባቸው በመሆኑና ያልተቋረጠ ክብካቤ የሚሹ መሆናቸውን በመገንዘብ ሠራተኛው በተከላው ላይ ያሳየውን ንቁ ተሳትፎ ችግኞቹን ለማሳደግ በሚደረገው ክብካቤም እንዲቀጥል



> አገራዊ ራዕይ " በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ፣ መልካም አስተዳደር የሰፈነባትና ማኅበራዊ ፍትህ የነገሰባት ፣ ከድህነት ተላቅ መካከለኛ ገቢ ያላት አገር እውን ማድረግ "

እሳስበዋል::

በሁለት ዛፍ ለሁለት ሺህ የችግኝ ተከላ ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ሚሌኒየም በዓል ዝግጅት ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ኪሮስ ህይለስላሴ በበኩላቸው የደን ሀብት መመናመን ያስከተለውን ጉዳት ከአመዝሔና ሠራተኞቹ በላይ የሚያውቅ የለም:: የደናችን መራቆት ለድርቅ አደጋ እያጋለጠን የመገኘቱን ያህል አደጋውን ለመቋቋም በግንባር ቀደምነት የተሰለፉት አመዝሔና ሠራተኞቹ ለችግኝ ተከላው ፕሮግራም ስኬት ያሳዩት ንቁ ተሳትፎ ስለችግሩ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያመለክትና የሚያስመሰግናቸው ነው ብለዋል:: ችግኞቹን ለተገቢው ደረጃ ለማድረስ በሚደረው ክብካቤም መላው ሠራተኛ ለሌሎች አርአያ በመሆን የበለጠ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ያላቸውን ዕምነት ገልፀዋል::

የአመዝአና ተጠሪ መ/ቤቶች የሚሌኒየም ዝግጅት አስተባባሪ አቶ ሲሳይ ታደሰ በዚሁ ወቅት እንደገለፁት የአመዝሔ ሠራተኞች አደጋ በደረሰባቸው አካባቢዎች ፈጥኖ በመገኘት እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታዎች በማለፍ ወገኖችን እንደሚታደጉ ሁሉ ዛሬም ለድርቅ ዓይነተኛ መንስዔ ከሆኑት አንዱ የደን መራቆትን ለመከላከል ሁለት ዛፍ በ2 ሺህ በሚለው መርህ ለመትከል መዘጋጀታቸው ተፈጥሮን ለመንከባከብ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያል ብለዋል:: አያይዘውም የተከልናቸውን ችግኞች በመንከባከብ ለትውልድ በቅርስነት በማቆየት የተፈጥሮ ሀብታችንን በመጠበቅ የበኩላችንን ድርሻ ለማበርከት ቃል እንገባለን ብለዋል::

በዚህ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም ላይ 550 የሚሆኑ የኤጀንሲውና የተጠሪ መ/ቤቶች ሰራተኞች ከ 2,000 ችግኞች በላይ መትከላቸው የታወቀ ሲሆን ፣ በተመሳሳይ ሐምሌ 15 ቀን 1999 ዓ.ም የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በሆለታ ባዘጋጀው የሚሌኒየም ችግኝ ተከላ ላይ የኤጀንሲውና የተጠሪ መ/ቤቶች ከ500 በላይ ሠራተኞች ከ3,000 በላይ ችግኞችን መትከላቸው ይታወሳል::